ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

ቀን/Date 1 ነሀሴ 06 2016

ቁጥር/ Ref. No. ጠ11-46/350

ለፌዴራል ጠበቆች ማህበር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) ለማዘጋጀት የሚረዳ መጠይቅ ማስሞላትንና ግብዓቶች እንዲላኩ መጠየቅን ይመለከታል</u>

በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ላለፉት አስር አመታት በሁሉም የፌዴራል እና የክልል ፍ/ቤቶች በመተግበር ላይ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል::

ይሁንና መመሪያው መሻሻል ያለበት መሆኑ ታምኖበት በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የማሻሻል ስራው በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑና በሂደቱም የፌዴራል ጠበቆችን ያማከለ መረጃ የማሰባሰብ እና ጥናት የማድረግ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ለዚህ ይረዳ ዘንድ በአባሪ የተያያዘውን 09 ገፅ "በጠበቆች የሚሞላ መጠይቅ" ፣በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያው ላይ ልምድ ላላቸው ጠበቆች በማስሞላት ፤ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን አስመልክቶ ለስልጠና እና ውይይት የተዘጋጁ ጽሁፎች፣ የምርምር ወረቀቶች ካሉም በመጨመር ፣ ሰካን (scan) አድርጋችሁ እስከ ነሐሴ 20 ቀን 2016 ዓ/ም ድረስ ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ጽ/ቤት፣ በ bantedirribaaf2017@gmail.com የኢ-ሜይል አድራሻ እንድትልኩ እንጠይቃለን::

ከሠላምታ ጋር

ዲሪባ ፈዬራ ቡልቲ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ

<u>ግልባጭ:-</u>

- ለፕሬዝዳንት ጽ/ቤት (ያለአባሪ)
- ለም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት (ያለአባሪ)
- ለፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ (ያለአባሪ)
- ለወንጀል ፍትህ ማሻሻያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (ያለአባሪ)

<u>ፌ/ጠ/ፍ/ቤት (ያለአባሪ)</u>

ስልክ/Tel. +251 111 553400
ፋክስ/Fax +251 111 550278
ፖ.ሳ.ቁ/P.O.Box 6166
www.fsc.gov.et

በጠበቆች የሚሞላ መጠይቅ

በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 88(4) ስር የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) እንደሚያወጣ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መጠይቅ የሚሰበሰበው መረጃ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስራ ላይ ያለውን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በማሻሻል ለሚያወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቀረፃ ተግባር የሚውል ይሆናል፡፡

ምላሽዎትን በምርጫ መልክ የቀረቡ ጥያቄዎችን ከአማራጮች ፊት ለፊት ያሉትን ፊደላት በማክበብ ወይም ልዩ ምልክት በማድረግ ፤ ማብራሪያ ለሚጠይቁ ጥያቄዎች ደግም ምላሽዎን ከጥያቄዎቹ በታች ባለው ክፍት ቦታ በማስፈር እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ክፍት ቦታ/ወረቀት በመጠቀም እንዲያሰፍሩ እንጠይቃለን፡፡

ስለፈቃደኝነትዎ እና ስለሰጡን ጊዜ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

መጠይቁን የሞሉት ጠበቃ

- የጠበቃው ስም (በፈቃደኝነት የሚሞላ) ....
- ያለዎት የጥብቅና ፈቃድ ዓይነት/ደረጃ ....
- የጥብቅና የአገልግሎት ዘመን ....
- የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያን በተመለከተ ያቀረቡት ጽሁፍ፣ የሰጡት ስልጠና፣ ወይም በሰልጣኝነት የተሳተፉ ከሆን ዝርዝሩን ይግለጹ
  ....
  ....
  ....
  ....
  ....
  ....
-

ክፍል-1 አጠቃላይ ጥያቄዎች

1. የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ሥራ ላይ በቆየበት ባፉት አስር ዓመታት የፍርድ ቤቶችን የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነት እና ወጥነት ለማረጋገጥ አስችሏል? አላስቻለም የሚሉ ከሆነ ምክንያቱን በዝርዝር ይግለጹ፡፡

2. ከሀገሪቱ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች እና መርሆች (በጠቅላላ ክፍሉ እንዲሁም በልዩ ክፍሉ ከተመለከቱት) ጋር አብሮ አይሄድም፣ ስለሆነም ሊሻሻል ይገባል የሚሉት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ድንጋጌ ካለ ከምክንያቱ ጋር ይግለጹ፡፡

3. የወንጀል መነሻ ቅጣት ስለሚወሰንበት ሁኔታ እንደወንጀሉ ክብደት በመመሪያው ደረጃ ለወጣላቸው ወንጀሎች በመመሪያው መሰረት ሲወስን ያጋጠመዎት (ያስተዋሉት) ተግዳሮት አለ? በዚህ ረገድ ቢሻሻል የሚሉትን ጨምረው ቢገልጹ፡፡

4. የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች አያያዝና ቅጣቱ የሚሰላበትን ሁኔታ አስመልክቶ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በአጠቃላይ ሊሻሻሉ ይገባል ብለው ያምናሉ? ከሆነ ምክንያቱን ይግለጹ፡፡

5. በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያው ያልተካተተ ነገር ግን ሊካተት ይገባል የሚሉት ካለ ቢገልጹ? ለምሳሌ እንደ ቅጣትን መገደብ፤ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚወሰን ቅጣት፤ ወዘተ....

6. በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 27 መሰረት ከመመሪያው ውጪ ቅጣት እንዲወሰን ለፍ/ቤት አመልክተው ያውቃሉ? ሌሎች ጠበቆች በዚህ ረገድ ያቀረቡት አስተያየት መኖሩንስ ያስታውሳሉ? በማመልከቻው በምክንያትነት የተጠቀሰውን ጨምረው በዝርዝር ቢገልጹ፡፡ (ከተቻለ ጉዳዩ የታየበትን ፍርድ ቤትና የመዝገብ ቁጥር ይጥቀሱ)

7. ብዳኞች (በፍርድ ቤቶች) መካከል በቅጣት አወሳሰን ማንዋሉ መሰረት ያለመስራት ልምድ አስተውለዋል? ከሆነ ምክንያቱ ምንድ ነው ይላሉ? የተወሰዱ ዕርምጃዎች ካሉም ይግለጹ፡፡

ክፍል 2 - የቅጣት ተመጣጣኝነት

8. በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ እና እርከን ከወጣላቸው ወንጀሎች ውስጥ፣ ለወንጀል ድርጊቶቹ የተቀመጠው ደረጃ እና እርከን ዝቅተኛ በመሆኑ ከወንጀል ክብደት አንፃር ተመጣጣኝ ቅጣት ለመጣል አያስችልም የሚሏቸው ወንጀሎች ካሉ ይግለፁ;

----

9. በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ እና እርከን ከወጣላቸው ወንጀሎች ውስጥ ለወንጀል ድርጊቶቹ የተቀመጠው ደረጃ እና እርከን ከፍተኛ በመሆኑ ተመጣጣኝ ቅጣት ለመጣል አያስችልም የሚሏቸው ወንጀሎች ካሉ ይግለፁ፡፡

----

10. በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በተለይ ጠቅላላ እና ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አያያዝ ላይ ያስተዋሏቸው ችግሮች ካሉ ይግለፁ፡፡

11.በቁጥር በርካታ[1] በማስረጃ የተደገፉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች (በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት) በሚኖሩ ጊዜ፣ የእነኚህ ምክንያቶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ያላቸውን ተቀባይነት ምን መሆን አለበት ብለው ያስባሉ?

(ሀ) በቀረቡት ማቅለያዎች ብዛት ልክ ሁሉም እንደ ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያ ይወሰዱ፡፡ (በመመሪያው ከተቀመጠው ገደብ ሳላልፍ)፡፡

(ለ) ሁሉንም አንድ ላይ በማጠቃለል እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ብቻ ይወሰዱ

(ሐ) የቀረቡትን ምክንያቶች በዘርፍ (በዓይነት) በመመደብ (thematic classification) በተገኘው ቁጥር ልክ ማቅለያ ይወሰድ ፡፡

(መ) ሌላ ምልከታ ካለ ይግለፁ ....

12.በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በተለይ ጠቅላላ እና ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አያያዝ እና ቅጣት አወሳሰን ላይ ያስተዋሏቸው ችግሮች ካሉ ይግለፁ፡፡

[1] ማብራሪያ ለምሳሌ፤- የሚከተሉት እና ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች በማስረጃ ተደግፈው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዙ ቢቀርቡልዎ
1) አገራዊ/ብሄራዊ ፕሮጀክቶች እና የልማት ስራዎች ላይ የተደረገ አስተዋፅኦ፤
ማህበራዊ አገልግሎቶች እና/ወይም በጎአድራጎት ተግባራት ላይ የነበረ ተሳትፎ
2) የጤና ችግር ያለበት መሆኑን
3)የልጆች አባት/እናት/ ወይም የቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለመሆኑ
4) የተከሳሽ ተማሪ መሆን
5) የተከሳሽ እድሜ ሁኔታ በእድሜ የገፋ መሆን
6) የተከሳሽ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ፣ ለ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ወዘተ ...

13.የገንዘብ (የብር) የመግዛት አቅም በመውረዱ (የዋጋ ግሽበት) ምክንያት በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ቅጣት በመወሰን ረገድ ችግር ፈጥሯል ይላሉ?

(ሀ) አዎ ፈጥሯል

(ለ) የለም አልፈጠረም

14.ከላይ በቁጥር 13 ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎፈጥሯል" የሚል ከሆነ ችግሩን ለመፍታት ያቀረቡት መፍትሄ (ክርክር ሊሆን ይችላል) ምን እንደነበር ይግለፁ?

15.ሌሎች ቅጣትን ተመጣጣኝ (ትክክለኛ) እንዲሆን ከማድረግ አንጻር በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ያስተዋሏቸው ችግሮች ካሉ ይግለፁ፡፡

ክፍል -3- ከእስራት በመለስ ያሉ ቅጣቶች በአማራጭ ስለመጠቀም

16.የወንጀል ህጉንና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ በእስራት ምትክ ከእስራት በመለስ ያሉ ሌሎች ዋና (መደበኛ) ቅጣቶች (የግዴታ ስራ ፣ የገንዘብ ቅጣቶች) እንዲወሰኑ ለፍ/ቤት አመልክተው ያውቃሉ?

(ሀ) አዎ አውቃለሁ

(ለ) የለም አላውቅም

17.ከላይ በቁጥር 16 ለቀረበው ጥያቄ ምላሽዎ "አዎ አውቃሁ" ከሆነ በምን ዓይነት ወንጀል/ሎች? ከእስራት ይልቅ አማራጭ ቅጣቱ/ቶችን እንዲመረጡ ያቀረቡት ምክንያት ምን ነበር? በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ከሆነ የተጣለው አማራጭ ቅጣት ምን ዓይነት ነበር?

18.በእስራት ምትክ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 122(2) መሰረት ተጨማሪ ቅጣቶች (ማስጠንቀቂያ፣ ተግሳጽ፣ ጥፋተኛው የሚጠይቀው ይቅርታ) በዋናው ቅጣት ምትክ እንዲወሰኑ ለፍ/ቤት አመልክተው ያውቃሉ?

(ሀ) አዎ አውቃለሁ

(ለ) የለም አላውቅም

19. ከላይ በቁጥር 18 ለቀረበው ጥያቄ ምላሽዎ "አዎ አውቃሁ" ከሆነ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደነበር ይግለጹ፡፡

20.ከላይ በቁጥር 16 እና 18 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽዎ "የለም አላውቅም" የሚል ከሆነ ከ እስራት በመለስ ያሉትን ቅጣቶች እና በእስራት ምትክ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 122(2) መሰረት ተጨማሪ ቅጣቶች በአማራጭ ይወሰኑ ዘንድ እንዳያመለከቱ ያደረግዎት ምክንያት ምንድን ነው? ያብራሩ፡፡

----

21. በስራ ላይ ያለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከእስራት በመለስ ያሉ ሌሎች ዋና (መደበኛ) ቅጣቶች እንዲሁም ተጨማሪ ቅጣቶችን ለዋናው ቅጣት ምትክ አድርጎ ለመወሰን አመቺ ነው ብለው ያስባሉ? ቢያብራሩልን፡፡

ክፍል 4 - ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎችን በተመለከተ

22. በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት መነሻ እርከን አወሳሰንን አስመልክቶ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የቅጣት አስተያየት ሲያቀርቡ የገጠመዎት ተግዳሮት አለ? በዚህ ረገድ መመሪያው ሊሻሻል ይገባል የሚሉት ካለ አካተው ይግለጹ፡፡

23. በመመሪያው ደረጃ ያልወጣላቸው ነገር ግን ደረጃ ሊወጣለት/ላቸው ይገባል ብለው የሚያስቡት የወንጀል ዓይነት/ ዓይነቶች አሉ? ካሉ የትኞቹ ናቸው? ለለዩት የወንጀል አይነት ደረጃ ማውጣቱ ለምን አስፈላጊ እንደሚሆን ጨምረው ይግለጹ፡፡

24.ከላይ በቁጥር 23 ለቀረበው ጥያቄ ምላሽዎ ደረጃ ሊወጣለት/ላቸው የሚገቡ የወንጀል ዓይነት/ ዓይነቶች አሉ የሚል ከሆነ ለለዩት የወንጀል አይነት ደረጃ በሚወጣበት ጊዜ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸውን ነገሮች በዝርዝር ይግለጹ፡፡

<u>ክፍል 5 - ልዩ ልዩ</u>

25. በመመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት በማቅረብ እንዲሁም ለቅጣቱ አወሳሰን የሚረዳ ማስረጃ በማቅረብ ረገድ የገጠመዎት ችግር አለ? በዚህ ረገድ መመሪያው ሊሻሻል ይገባል የሚሉበት ምክንያት ካለ ጨምረው ይግለጹ፡፡

26.ከፍ ሲል ከተጠቀሱት በተጨማሪ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ሊሻሻል ይገባል የሚሉበት ሌላ ምክንያት/ቶች ካሉ ይግለጹ፡፡

በድጋሚ እናመሰግናለን